news ITEMS

የአሜሪካን ቤተ መጻሕፍት ።
በቀ. ኃ. ሥ. ጐዳና
አዲስ ፡ አበባ ።

United States Information Center
Haile Selassie Ist Avenue
Addis Ababa

ወሬ፤

አዲስ አበባ (ሐምሌ 4-1952) ወደ ኮሪያ ከተላከው የኢትዮጵያ የክቡር ዘበኛ ጦር ውስጥ ከጠላት ጋር በገጠመው የሰነረኛ ጦርነት የሻለቃ ታደሰ ወንድምአገኘሁ ባደረጉት ታላቅ የጀግንነት ሥራ የዩናይትዱ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ፕሬዚዳንት አይዘንሃወር የተሰጠ የ ክብር ሜዳይ ፤ሜሪት፤ እንደሸለሙዋቸው፤

እ፡ ኤ፡ አቆጣጠር ሐምሌ 4 ቀን 1952 ዓ ም የአሜሪካኖች የነጻነት በዓል በሚከበርበት ቀን አዲስ አበባ በሚገኘው የአሜሪካን ኤምባሲ ውስጥ ጉዳይ ፈጻሚ በሚስተር ሪቻርድ ጂ ገትውድ እጅ ይህ የተባለው ሜዳይ ለሻለቃ ታደሰ ወንድምአገኘሁ ይሰጧቸዋል፡፡

የሻለቃ ታደሰ የፈጸሙት የጀግንነት ሥራ ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው ነው፡፡

ስነ ሥርዓቱ ከፍተኛ የጦር ሹማምንቶች ባሉበት ይፈጸማል፡፡

፤ እ፡ ኤ፡ አቆጣጠር ከሰኔ 27 ቀን እስከ ጥቅምት 4 ቀን 1951 ድረስ የቃኘው ሻለቃ ጦር አዛዥ ሆነው በፈጸሙት ጦርነት ውስጥ የሻለቃ ታደሰ ስራቸው ሰፍቷል የጀግና ስም አስጠራ፡፡ ብልሁ በሆነው የጦር መሪነትና መሪውን በነቃ ም ስጠራዊ አስተዋይ አስተዳደርነት ወታደሮች ከዚህ በፊት በማያውቁት አገር ውስጥና እንዲሁም በ ያሉዋቸው አዲስ በሆኑ ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያዎች በመጀመሪያ ጊዜ በገጠሙት ጦርነት ባልተለመደ ታ. ቲ. የሻለቃውን ጦር በጠላት ላይ ድል ለማግኘት አበቁት፡፡ የጃንጁ ያለመሸነፍ፣ ያህል ልዩነት እንቢ እያለ ብልሃት በተሞላ ትእዛዝ ወታደሮችን በማዘዝና በመምራት ከጦሩ ጓደኞች ወታደሮች ጋር አብሮ በመዋጋት በኮሪያ ውስጥ በጣም ኃይለኛ የሚሆኑ ጦርነቶች በተደረገበት ጊዜ የቃኘው የሻለቃ ጦር አብሮት ይዋጋ ለነበረው ለሰላሳ ሁለተኛው እግረኛ ሬጅመንት ታላቅ ደጋፊ ሆኖ የድል መንሣትን እድል አስገኘው፡

የሻለቃ ታደሰ ለሕይወታቸው ባለመስጋትና ባለመሣሣት በፈጸሙዋቸው ተገቢ ተግባሮች በኮሪያ ውስጥ ለጦር ጓደኞች ወታደሮች ድል ለማስገኘት በላይ ለሠራዊታቸውና ለአገራቸው ክብር አስገኝተዋል፤፤ ፡